# <u>መድረኩ በሲያትል ባደረገዉ ስብሰባ ዙሪያ - አማኑዌል ዘሰላም</u>

(amanuelzeselam@gmail.com)

መስከረም 11 2005

የመድረክ ከፍተኛ አመራሮች ከጥቂት ሳምንታት በፊት በሲያትል ህዝባዊ ስብሰባ ማድረጋቸው ይታወሳል። ኢትዮሜዲያ የ«መድረክ ፈተና» በሚል፣ በስብሰባው የተገኙ አንዳንድ ወገኖች፣ በመድረኩ አመራር ላይ ያቀረቡትን ጠንካራ ትችቶች ያዘለ፣ ቪዲዮ ለአንባቢያኑ አቅርቧል።

«የመድረክ አመራሮች ምን ቢሉ ነዉ ይሄን ያህል ተቃውሞ የደረሰባቸው ?» የሚል ጥያቄ ብዙዎቻችን ሳንጠይቅ እንደማንቀር አስባለሁ። በዚህም ምክንያት ይመስለኛል አቶ ስዬ ኢትዮጵያዉያን ግልጽ መረዳት ይኖራቸዉ ዘንድ፣ የንግግራቸዉ ሙሉ ይዘት በየድህረ ገጾቹ ይፋ እንዲሆን ያደረጉት።

ኢሳት የተሰኘው የዳይስፖራ ቴሌቭዥን፣ መድረኩ በሲያትል ባደረገዉ ስብሰባ ዙሪያ ሰፊ ዘገባ አቅርቧል። የኢሳት ጋዜጠኛ አቶ ሲሳይ አጌና እንዲሁም ተጋብዘዉ አስተያየት እንዲሰጡ የተጠየቁትና የቀድሞ የኢሕአዴግ ባለስልጣን የነበሩት፣ አቶ ተስፋዬ ገብረአብ፣ በተለይም በአቶ ስዬ ላይ ጠንካራ ትችት አቅርበዋል። አቶ ስዬ፣ ችግራቸው ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር እንጂ ከስርዓቱ ጋር እንዳልሆነ፣ የትግራይ ብሄረተኝነትን አቀንቃኝ እንደሆኑ ነበር፣ የኢሳት አድማጮችን ለማሳመን እነዚህ ጋዜጠኞች ሲሞክሩ የተሰሙት።

ብዙ ጽሁፎችን በማበርከት ከሚታወቁት ኢትዮጵያዊ መካከል አንዱ አቶ ይልማ በቀለ ናቸዉ። «Seeye and his politics» በሚል ርእስ አቶ ይልማ አንድ ጽሁፍ አስነብበዉናል። ከወቅቱ ሁኔታዎች ጋር የማይገናኙ የተለያዩ ሃሳቦችን፣ እህል በጀንያ እንደሚታጨቅ አጭቀዉ ፣ በአቶ ስዬ ላይ ይሄ ነዉ የማይባል ናዳ ነዉ ያወረዱት። «Seeye has to stop treating us like imbeciles and go join his old party if that is what he wants since his nemesis is gone. One cannot be a supporter of a narrow ethnic based party while at the same time sitting as a leader of a multi-national organization.» ሲሉ ነዉ፣ ምንም አይነት ድጋፍ ለአቶ ስዬም ሆነ አባል ለሆኑበት ድርጅት (አንድነት/መድረክ) መስጠት እንደሌለበት የሚከራከሩት። አገር ቤት የሚደረገዉ ትግል ካልተረዳ ማን ሊረዳና ሊደገፍ እንደሚችል አቶ ይልማ በዚሁ አጋጣሚ ቢያብራሩልን ጥሩ ይሆን ነበር።

አዜብ ጌታቸዉ በሚል ስም የጻፉ ሌላ ኢትዮጵያዊ ደግሞ «መለስ ስለሞቱ የስዬ ጎራዴ ወደ እፎቱ» በሚል ርእስ ባስነበቡን ጽሁፍ በተመሳሳይ ሁኔታ አቶ ስዬ ፣ ጠባቸው ከአቶ መለስ ጋር ስለነበረ፣ አቶ መለስ በመሞታቸው የርሳቸዉ ትግል እንዳበቃለት ሊነግሩን ሞክረዋል። «አቶ ስዬ የአንድነት ፓርቲን የተቀላቀሉት በአንድነት ፓርቲ መርህዎች አምነዉ ሳይሆን፣ ስዉር ዘረኛና ብሄረተኛ አጀንዳቸዉን ለማሳካት ሲሉ ነው» በማለትም ወገዛ መሰል ክስ ሰንዝረዋል።

አቶ ስዬ ላይ ትችቶች ለምን ቀረቡ አልልም። እንደ ዜጋ የፖለቲካ መሪዎችን መጠየቅና ማፋጠጥ ያስፈልጋል። ገንዘብ ሲሰበስቡ፣ ሰብሰባ ሲጠሩ፣ እንዲሁ በስሜት ተነድተን «ሆ» ብለን መደገፍ የለብንም። «500 ዶላር አዋጡ ሲሉን ለምን ? ከዚህ በፊት ያዋጣነዉስ የት ሄደ ? » ብለን መጠየቅ አለብን። እንድንደግፋቸው ከፈለጉ ከወሬ ያለፈ የተጨበጠ ነገር ሊያሳዩን ያስፈልጋል። ፖለቲከኞችን ለሚሰሩትም ሆነ ለሚናገሩት ነገር ተጠያቂ ማድረግ ሊለመድና ሊዘወተር የሚገባ ትልቅ ጉዳይ ነዉ።

የመድረክ አመራር አባላት መጠየቅ የነበረባቸው በርካታ ጠቃሚና አንገብጋቢ ጉዳዮች ነበሩ። እንግዲህ ቅሬታዬ ጠቃሚ አጀንዳዎች ላይ ማተኮር ሲገባ ለምን ምናምንቴዉ ላይ እንዘፈቃለን የሚል ነዉ።

«በአገራችን ኢትዮጵያ የመንግስት ሽግግር በሚደረግበት ወቅት፣ በአገር ዉስጥ መሰራት የሚኖርባቸው ጉዳዮች እያሉ፣ የመድረክ አመራር አባላት እዚህ በዉጭ አገር ምን ያደርጋሉ ? ይኸዉ ከተቋቋመ አምስት

አመታት አለፉ። የኢሕአዴግ የዘር ድርጅቶች ሕብረ ብሄራዊ ለመሆንና ለመዋሃድ በወሰኑበት ጊዜ፣ የመድረክ ድርጅቶች ለምን መዋሃድ አልቻሉም ? የፌዴራል አወቃቀር ምን መሆን እንዳለበት፣ የቡድን እና የግለሰብ መብቶች ቢጋጩ ለየቱ ቅድሚያ እንደሚሰጥ በመሳሰሉ መሰረታዊ በሆኑ ጥያቄዎች ላይ የጠራ አቋም ለምን እስካሁን እንደ መድረክ አልያዙም ? ስልጣን መድረኩ ቢይዝ አገር የማስተዳደር ብቃት አለው ወይ ? ..» የመሳሰሉ አንገብጋቢ ጥያቄዎችን መጠይቅ ሲገባ፣ የማይረቡ፣ ቁንጽልና ስሜታዊ የሆኑ አጀንዳዎችን እያነሳን ባዶ ነገርን ማኘክ ተገቢ አይመስለኝም።

አቶ ስዩ በሲያትል ያደረጉትን ንግግር አንብቤዋለሁ። የጻፉትን በሰከነና በተረጋጋ ሁኔታ ካጤንነዉ ትልቅ ትምህርት የሚሰጥና ጠቃሚ ሃሳቦችን ያዘለ ንግግር እንጂ የሚያስኮርፍ፣ የሚያናድድና ጦር የሚያስመዝዝ አልነበረም።

## <u>አቶ ስዬና ሱዛን ራይስ</u>

አቶ ስዬ በንግግራቸው መዝጊያ በተቃዋሚዎችና በዲያስፖራው በኩል ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ የሚሏቸውን ጥቂት ነጥቦችን አስቀምጠዋል። ከነዚህም ነጥቦች መካከል አንዱ በዲፕሎማሲዉ ዘርፍ፣ በተለይም በዳያስፖራዉ ትልቅ ሥራ መሰራት እንዳለበት የጠቆሙት ነዉ።

የአሜሪካ ከፍተኛ ባለስልጣን የሆኑት ዶር ሱዛን ራይስ፣ በአቶ መለስ የቀብር ስነ-ስርዓት ላይ ባደረጉት ንግግር ብዙዎቻችንን አስከፍተዋል። የአቶ መለስ ተቃዋሚዎችን ደደቦችና እብዶች (Fools and Idiots) ነዉ ያሏቸዉ። ይህ አይነቱ ንግግር፣ በርግጥ ከአንድ ዲፕሎማት አይጠበቃም። የሴትዮዋን ትንሽነት ያሳየ ነዉ።

አንድ የዩኒቨርሲቲ መምህር ወዳጅ አሉኝ። ደወሉልኝና «ሱሳዝ ራያስ ሰደበችን አይደለ ? ናቀችን አይደለ ? » አሉኝ። መልሴ ቀጥተኛና ፈጣን ነበር። «ታዲያ መናቅ አይገባንም እንዴ ? » አልኳቸው። ለጥቂት ጊዜ ዝም አሉና «ትክክል ነህ» አሉኝ።

በውጭ አገር ያሉ ተቃዋሚ ነን የሚሉ በአንድ ድምጽ አይናገሩም። ስብሰባዎች ይደረጋሉ፣ በየራዲዮ ቴሌቭዥኖች ብዙ ይወራል። ግን የዲፕሎማሲን ሥራ በተመለከተ በተቀናጀ፣ ዉጤት በሚያመጣ መስኩ ስራ አልተሰራም። እዉነት እንነጋገር ከተባለ ዳያስፖራው በዲፕሎማሲዉ ረገድ የሚሰጠዉ ዉጤት «F» ነዉ።

እንግዲህ ይሄ እንዲለወጥ ነዉ አቶ ስዬ አርመኖችን እንደምሳሌ በመጥቀስ አስተያየታቸዉን የሰጡት። «ወ/ሮ ሱዝን ራይስ በአቶ መለስ ቀብር ላይ ሰውየውን በማድነቅ የሰጡት ዲስኩር የተጋነነ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ተኩረት ሊሰጠው ይገባ የነበረው ግን ከአቶ መለስ በኋላ ከሚኖረው መንግስት ጋር አሜሪካ ሊኖራት የሚገባው ግንኙነትን አስመልክቶ ምን አሉ የሚለው መሆን ነበረበት፡፡ ዴሞክራሲ ሰብአዊ መብትና ነጻ ፕሬስ ላይ መሻሻል እንዲኖር አሜሪካ የምትጠብቅ መሆኑዋን የመለከተ መልእክታቸውን መዞ በማውጣትና በዚሁ አስታኮ መደረግ ያለበትን መጠቆም ላይ ማተኮር በተገባ ነበር፡፡» ሲሉ ነዉ እንዲሁም በንዴትና በብስጭት ተነሳስተን ስሜታችንን የሚያረካ ፣ ግን ዉጤት የማያመጣ ተግባራት ላይ ከምንሰማራ ፣ ምራቃችንን ዋጥ አድርገን፣ ለጊዜው ብንሰደብም የወደፊቱን በማለም፣ ዉጤት በሚያመጣ መልኩ የዲፕሎማሲ ሥራ መሰራት እንዳለበት የመከሩት።

ምናልባት እንደ አና ጎሜዝ ካሉ ጥቂቶች በስተቀር ፣ ሱዛን ራይስን ጨምሮ ብዙዎች የአዉሮፓና የአሜሪካ ባለስልጣናት ለተቃዋሚዉ ከበሬታ እንደሌላቸው መርሳት የለብንም። በዲፕሎማሲዉ ረገድ ያለ ምንም ማጋነን ኢሕአዴግ ተቃዋሚዎችን በልጧል።

ታዲያ ይሄ ሁኔታ መቀየር የለበትምን ? የሰለጠነ፣ ዉጤት የሚያመጣ፣ በመረጃና በማሳመን ላይ ያተኮረ ፣ ከስሜታዊነትና ከግብተኝነት የጸዳ ዲፕሎማሲ አያስፈልገንምን ? ይሄንን ነዉ እንግዲህ አቶ ስዬ እየመከሩ

ያሉት። (በነገራችን ላይ ዲፕሎማሲ ምን ማለት እንደሆነ የበለጠ ለመረዳት አምባሳደር ዘዉዴ የኤርትራ ጉዳይ በሚል መጽሃፋቸዉ ያሰፈሩትን፣ እነ አክሊሉ ሃብተወልድ፣ ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለማዋሃድ ሲያደርጉ የነበሩትን አስደናቂና ጥበብ የተሞላበት የዲፕሎማሲ ሥራ ማየት ይቻላል)

**አቶ መለስ የጀመሯቸዉን መልካም ተግባራት መቀጠል !**

ከኢሕአዴግ ጋር የፖለቲካ ልዩነቶች እንዳላቸው የገለጹት አቶ ስዩ ላለፉት 21 አመታት የተከናወኑ መልካም ተግባራት መቀጠል እንዳለባቸው አስረድተዋል።

«ከኢህአዴግ ጋር የፖለቲካ ልዩነት ቢኖረንም እኛም የአገራችን ኢኮኖሚያዊ እድገት በጠንካራ መደላደል እንዲቆምና ቀጣይነቱ እንዲረጋገጥ እንፈልጋለን፤ የሃያ አንደ ዓመቱ ሰላም ተጠናክሮ እንዲቀጥልና አገራችን በክፍለ አህጉራችንና በአህጉራችን ሰላም የምትጫወተው ገንቢ ሚና ቀጣይና አስተማማኝ እንዲሆን እንሻለን፤ ሃገራችን በተፈጥሮ ሃብቷ ተጠቃሚ ትሆን ዘንድ የተጀመሩት ጅማሮዎች ቀጣይነትና ጥልቀት እንዲኖራቸውና ለዚሁ ስኬት ከአካባቢው አገሮች በምክክር መስራትዋን እንድትቀጥልበት እንፈልጋለን፡፡»ነበር ያሉት አቶ ስዬ።

መቼም በፖለቲካ አመለካከታችን ጭፍኖችና በጥላቻ የተሞላን ካልሆንን በቀር ኢሕአዴግ ያከናወናቸው መልካም ተግብራት የሉም ብሎ መናገር ትንሽ አስቸጋሪ ነዉ።

ሰሞኑን አልሻባብ የተሰኘው የሽብርተኛ ቡድን፣ በኢትዮጵያ ከሚታገዙ የአፍሪካ ሕብረትና በሶማሊያ ወታደሮች፣ በተቀናበረ መልኩ በደረሰበት ጥቃት እየተሸነፈ፣ ከሚቆጣጠረዉ የመጨረሻ የወደብ ከተማ ኪሲማዮ ለቆ እየወጣ ነዉ። ከጊዜ ወደ ጊዜ ለ22 አመታት የታመሰችዋ ሶማሊያ እየተረጋገች ከኢትዮጵያ ጋርም ያላትን ዝምድናና መቀራራብ እያጠናከረች በመምጣት ላይ ናት። በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ መንግስት የተደረገዉ ጥረት አዎንታዊና መቀጠል ያለበት ነዉ።

በሰሜን እና ደቡብ ሱዳን መካከል ጦርነት የበለጠ እንዳይፋፋም የሰላም አስጠባቂ ጦር በማሰማራት በአካባቢዉ መረጋጋት እንዲኖር ኢትዮጵያ የተጫወተችዉ ሚና የሚያኮራና ተጠናክሮ ሊደገፍ የሚገባዉ ነዉ።

በልማቱ አንጻር ከሄድን ደግሞ አባይን ለመገንባት ከሚደረገዉ ጥረት ጀምሮ፣ በአቶ መለስ ዘመን የተነደፉና የተጀመሩ በርካታ የልማት እንቅስቃሴዎች መቀጠል ይኖርባቸዋል። ትምህርት ቤቶች፣ ክሊኒኮች፣ መንገዶች፣ ግድቦች ሲሰሩ መቃወም ፣ እቀባ እንዲደረግ መጠየቅ ነዉር ነዉ።

አቶ ስዬ፣ ይሄንኑ በአብዛኛዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚደገፈዉን ኮመን ሴንስ አቋም ነዉ ያንጸባረቁት። ጠቃሚ ያልሆኑ የኢሕአዴግ ፖሊሲዎችን ለመቃወምና ለመታገል ዝግጁ መሆን እንደሚያስፈልገዉ ሁሉ፣ መልካም አጀንዳ ይዞ ኢሓዴግ ሲንቀሳቀስም አብሮ ለመስራት መዘጋጀት እንደሚያስፈልግ ነዉ ያስረዱት። ይሄ ደግሞ ይብዛም ይነሰም የሰለጠነ ፖለቲካ ነዉ።

**ለሃያ አንድ አመታት አለ ስለተባለዉ ሰላም**

ላለፉት ሃያ አንድ አመታት ሰላም እንደነበረ አቶ ስዬ ተናግረዋል። ይሄንን ሲሉ ዜጎች አልሞቱም፣ ዜጎች አልታሰሩም፣ መብት አልተረገጠም ማለታቸዉ አይመስለኝም። እርሳቸዉ እራሳቸዉ ካለፉት ሃያ አንድ አመታት አንድ ሶስተኛዉን በቃሊቲ ነዉ የነበሩት።

ነገር ግን በሶማሊያ፣ በኮንጎ፣ በሲሪያ፣ በሱዳን የምናየዉን፣ በደርግ ጊዜም በአገራችን የነበረዉን አይነት የርስ በርስ ጦርነትና ፍጭት አልነበረም ማለታቸዉ ነዉ። እስከሚገባኝ ድረስ የኦጋዴን ነጻ አወጭ ግንባር አልፎ አልፎ ካደረሰዉ ወታደራዊ ጥቃት በስተቀር፣ ይሄ ነዉ የሚባል፣ ዉጭ አገር ዘራፍ በሚሉ

ድርጅቶች አነሳሽነት፣ የተሰማ ተኩስም ሆነ ወታደራዊ ግብግብ አልሰማንም። ስለዚህ በአንጻራዊነት ሰላም ነበር ማለታቸዉ የተሳሳቱ አያስበላቸውም።

## ከኢሕአዴግ ጋር ስለመነጋገር

አቶ ስዬ፣ ከኢሕአዴግ ጋር መነጋገር፣ መግባባትና መቀራረብ ያስፈልጋል በሚሉበት ጊዜ፣ አንዳንዶች እንደሚከሱት አቶ መለስ ስለሞቱ ያመጡት አዲስ አቋም በጭራሽ አይደለም።

ገና ከእሥር ቤት እንደወጡ፣ ለአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ የተናገሩት ነገር ነበር። በኢሕአዴግ እና በተቃዋሚዎች መካከል እንደ ድልድይ ሆነዉ እርቅ ለማምጣት እንደሚሰሩ ነበር ያኔ የተናገሩት።

«ዘረኛ ናቸዉ። ለኢትዮጵያ ሳይሆን ለትግራይ ብሄረተኝነት የቆሙ ናቸው» ተብሎ እየቀረበባቸው ላለዉ አሳዛኝና አሳፋሪ ክስም ምላሽ ይሆን ዘንድ ትንሽ ቃላት ልወርወር። በመጀመሪያ ደረጃ ትግራይ እንድትጠቀም መስራት፣ ጸረ-ኢትዮጵያዊነት አይደለም። ትግራይ ለማች ማለት ኢትዮጵያ ለማች ማለት ነዉ። በሁለተኛ ደረጃ አቶ ስዬ በሂደት የደረሱበት ደረጃ አለ። ከእሥር ቤት ሲወጡ የቀድሞ ጓዶቻቸው አረና ትግራይን እንዲቀላቀሉ ቢጠይቋቸዉም «ከሕወሃት አትማሩም ወይ? ከዘር ፖለቲካ አልፈን መሄድ አለብን » በሚል ነዉ የአንድነት ፓርቲን የተቀላቀሉት።

አቶ ስዬን ማጥቃት ከተፈለገ እንደዉ ቢያንስ ቢያንስ፣ ሴንስ የሚሰጥ መከራከሪያ ማቅረቡ ይሻል ነበር። መረጃን ይዘን፣ የተሻለ አማራጭ አቅርበን፣ የአቶ ሰዬን ሃሳቦች በሃሳቦቻችን መጣል ሲገባ ፣ እርስ በርሱ የሚጋጭ፣ እንደዉም እኛኑ እራሳችንን የሚያሳንስ፣ ዘረኞች መሆናችንን የሚያሳይ ተራ አሉባልታዎችን መወርወር ደካማነት ነዉ።

እንግዲህ አቶ ስዬ ግልጽ ያደረጉት ነገር አለ። አሁን በአገራችን አዲስ ጠቅላይ ሚኒስተር ተሾመዋል። እንደ ኢትዮጵያ ሪቪዉ ያሉ በገዢዉ ፓርቲ ላይ ጠንካራ ትችት በማቅረብ የሚታወቁ ወገኖች ለአዲሱ መንግስት ነጭ ባንዲራ እያውለበለቡ ነዉ።

በፊታችን የሚጠብቀን መንገድ ሲያመላክቱን «መንገዱ የይቅርታ፤ የመመካከር፤ የፍቅርና የአንድነት መንገድ ብቻ ነው። » ያሉን አቶ ስዬ፣ እርሳቸዉና ድርጅታቸዉ መድረክ ለሰላምና ለእርቅ ዝግጁ መሆኑ አብራርተዋል። «የኢህአዴግ ደጋፊ፣ የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊ፤ የዚህና የዚያ ብሄር ተወላጅ ወይም የዚያና የዚህ ሃይማኖት ተከታይ ሳንባባል ሁላችንም ለሁላችን እና ለአገራችን ድል በጋራ መስራት አለብን» ያሉት አቶ ስዬ፣ የከረረ ፣ ዜጎችን የማዋረድና የመሳደብ፣ ያለመቻቻል፣ የጥላቻና በስሜት የመነዳት ፖለቲካ እንዲቆም ጥሪ አቅርበዋል።

በጥላቻ፣ በእልህ በስድሳዎቹ ጊዜ እንደነበረዉ አይነት የስሜታዊነት ፖለቲካ (ሞብ ፖሊቲክስ) የተተበተቡ ወገኖች ይህንን ጥሪ ላይቀበሉ ይችላሉ። የመረጡትን መንገድ የመከተል ሙሉ መብታቸው የተጠበቀ ነዉ። እንደ አንድ ዜጋ ግን ለሰላምና ለእርቅ ድጋፌን እሰጣለሁ። መድረኩም በዚህ በሰላሙ መንገድ እንዲገፋበት፣ የሰላምና የእርቅ ወሬ የማይጥማቸዉ ወገኖች ለሚያሰሙትም ጩከት ቦታ እንዳይሰጥ እመክራለሁ።